## የህዝብ እርዳታ ችሎት ሲጠይቁ ምን ይከሰታል?

የማህበራዊ እና ጤና አገልግሎቶች (Department of Social and Health Services, DSHS) ጥቅማጥቅሞችን ለመከልከል፣ ለመለወጥ ወይም ለማቆም ሲሞክር አንድ ወገን ችሎት ሊጠይቅ ይችላል። ችሎቱ የሚካሄደው በአስተዳደራዊ ችሎቶች ቢሮ (Office of Administrative Hearings, OAH) ውስጥ ባለ ገለልተኛ ዳኛ ነው።

OAH የችሎቱ ቀን የሚካሄድበትን ቀን፣ ሰዓት እና ቦታን የያዘ የችሎት ማስታወቂያ በደብዳቤ ይልክልዎታል። በአማካይ፣ ችሎቶች ለ30 ደቂቃ ያህል ይቆያሉ።
(እስከ 60 ደቂቃዎች ድረስ ያቅዱ።)

**አድራሻዎ ወይም ስልክ ቁጥርዎ ከተቀየረ ወዲያውኑ ለOAH ይንገሩ።**

## ለችሎትዎ እንዴት እንደሚዘጋጁ

በችሎቱ ላይ እራስዎን መወከል ወይም ጠበቃ ወይም ሌላ ማንኛውንም ሰው እንዲወክልዎት መምረጥ ይችላሉ። (የDSHS ተቀጣሪ ላይመርጡ ይችላሉ)። ጠበቃዎ ለሚያስከፍሉዎት ማናቸውም ክፍያዎች እርስዎ ኃላፊነቱን ይወስዳሉ።

DSHS በአስተዳደራዊ ችሎት አስተባባሪ ሊወከል ይችላል። አስተባባሪው በእርስዎ እና በDSHS የቀረቡ ሰነዶችን ያካተተ የችሎት ጥቅልበደብዳቤይልኩልዎታል። የችሎት ጥቅልል በጥንቃቄ ያንብቡ እና በችሎቱ ጊዜ ከእርስዎ ጋር ይያዙት።

**ሰነዶችን ማስገባት (ኤግዚቢቶች)፦** ዳኛው እንዲመለከቷቸው የሚፈልጓቸው ሰነዶች ካሉ፣ ወዲያውኑ ወደ OAH እና የHCA ተወካይ ይላኳቸው።

ዳኛው እንዲያያቸው ሊፈልጓቸው የሚችሏቸው የሰነድ ምሳሌዎች፦

- ችሎት እንዲጠይቁ ያደረገዎት በDSHS የተላከልዎት ማስታወቂያ።
- የይገባኛል ጥያቄዎችዎ ትክክል መሆናቸውን የሚያሳዩ ሰነዶች።
- እንዲታዩ የሚፈልጓቸው የማናቸውም ልዩ ወይም የፋይናንስ ሁኔታዎች ማረጋገጫ።
- DSHS ለዳኛው ማሳየት እንዳለብዎት የነገሩዎት ሰነዶች። OAH መጠናቸው 2.0 ጊጋ ባይት (giga bites, GB) እና ከዚያ በላይ የሆኑ ሰነዶችን መቀበል አይችልም። OAH መጠናቸው 2.0 GB እና ከዚያ በላይ የሆኑ ሰነዶችን ውድቅ ያደርጋል።
- OAH በሚከተሉት ቅርጸት የሆኑ የቪድዮ ኤግዚቢቶችን መቀበል አይችልም፦ .mp4፣ .avi፣ .mpg፣ .mpeg። OAH በሌላ ማንኛውም ቅርጸት የገቡ የቪድዮ ኤግዚቢቶችን ውድቅ ያደርጋል።
- OAH በሚከተሉት ቅርጸት የሆኑ የኦዲዮ ኤግዚቢቶችን መቀበል አይችልም፦ .mp3። OAH በሌላ ማንኛውም ቅርጸት የገቡ የኦዲዮ ኤግዚቢቶችን ውድቅ ያደርጋል።

**ችሎታዎ በሚከተለው መንገድ ሊሆን ይችላል፦**

- **በስልክ ወይም**
- **በአካል**

**የችሎት ማስታወቂያ እንዴት መሳተፍ እንደሚቻል ያብራራል።**

የቃል አስተርጓሚ ከፈለጉ፣ OAH ያለምንም ወጪ ያቀርብልዎታል። አካል ጉዳተኛ ከሆኑ በችሎቱ ላይ ለመሳተፍ የሚያግዙዎትን ማስተካከያዎች መጠየቅ ይችላሉ። በችሎት ማስታወቂያዎ ላይ ወዳለው የOAH ቢሮ በመደወል የቃል አስተርጓሚ ወይም ማስተካከያ መጠየቅ ይችላሉ።

የችሎትዎ ጊዜ ወይም ቀን እንዲለወጥ መጠየቅ ከፈለጉ በተቻለ ፍጥነት የአስተዳደራዊ ችሎት አስተባባሪን ወይም OAH ያነጋግሩ። መርሐግብር በተያዘለት የችሎት ጊዜ ላይ ለውጥ መስጠት የሚችሉት ዳኛው ብቻ ናቸው። ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት፣ ዳኛው DSHS በጥያቄዎ መስማማቱን ወይም አለመስማማቱን ማወቅ ይፈልጋሉ።

- በቂ ምክንያት ከሌለዎት ዳኛው ጥያቄዎን ውድቅ ያደርጉታል።
- ዳኛው የችሎት ሰዓቱን ከለወጡ፣ በድጋሚ መርሐግብር በተያዘው ችሎት ጊዜ ጥቅም ላይ እንዲውል የችሎት ጥቅሉን ያስቀምጡ።
- የችሎቱ ውሳኔ እስኪወሰን ድረስ የቀጠሉ ጥቅማጥቅሞችን እየተቀበሉ ከሆነ እና የችሎቱን ቀን ለሌላ ጊዜ ለማስተላለፍ ከጠየቁ፣ የDSHS ተወካይ ጥቅማ ጥቅሞችዎ ይቀጥላሉ ወይም አይቀጥሉም የሚለውን ለመወሰን ዳኛውን ችሎት ሊጠይቅ ይችላል።

ዳኛው ጋር በአካል ችሎት ላይ የመገኘት መብት አለዎት። ችሎትዎ የሚካሄድበትን መንገድ ለመቀየር ከፈለጉ በችሎት ማስታወቂያ ላይ የተዘረዘሩትን የOAH ቢሮ ማነጋገር አለብዎት።

የሕግ ጥናት ለማድረግ ፍላጎት ካለዎት፣ አገናኞች www.oah.wa.gov እና www.washingtonlawhelp.org ላይ ይገኛሉ።

**የOAH ችሎት ናሙና ቪድዮን የሚተለው ላይ ይመልከቱ www.oah.wa.gov**
(በእንግሊዝኛ እና በስፓኒሽ ይገኛል)

የቅናሽ ዋጋ የተደረገላቸው የህግ ድጋፍ አማራጮች እነሆ:-

| የመርጃ ስም | ስልክ ቁጥር | ድር ጣቢያ |
|---|---|---|
| የተቀናጀ የህግ ትምህርት፣ ምክር እና ሪፈራል (Coordinated Legal Eduction, Advice and Referal, CLEAR):- በKing ካውንቲ ውስጥ | ወደ 211 ይደውሉ | www.wa211.org/region/king-county/ |
| CLEAR:- ከKing ካውንቲ ውጭ | 888-201-1014 | |
| የወታደሮች ፕሮጀክት | 855-6578387 | http://nwjustice.org/veterans |
| WA ግዛት የሕግ ባለሙያዎች ማህበር | | https://www.wsba.org/for-the-public/find-legal-help |

**ከችሎቱ በፊት ጉዳይዎን ለመፍታት መሞከር ከፈለጉ ወይም ስለ ደንቦቹ ጥያቄዎች ካሉዎት የDSHS አስተዳደራዊ ችሎት አስተባባሪን ማነጋገር ይችላሉ። አስተባባሪው የህግ ምክር ሊሰጥዎ አይችልም።**

## በችሎትዎ ውስጥ እንዴት እንደሚሳተፉ

**በስልክ የሚደረግ ችሎት:-** በችሎት ማስታወቂያ ውስጥ ያሉትን መመሪያዎች ይከተሉ። ካልተገኙ ወይም ካልተሳተፉ የችሎት መብትዎን ሊያጡ ይችላሉ።

- ማስታወቂያው ሊገኙበት የሚችሉበትን ስልክ ቁጥር እንዲያቀርቡ ሊያዝዎ ይችላል። ማስታወቂያው ለጉዳይዎ ልዩ የሆኑ የጥሪ ኮዶችን ሊሰጥዎ ይችላል።
- ጥሩ የስልክ ተቀባይ ሊኖርዎት ይገባል።
- እባክዎ ከታገደ የደዋይ መታወቂያ ጥሪዎችን መቀበል መቻል እንዳለብዎ ልብ ይበሉ።

**በአካል የሚደረግ ችሎት:-** ቢያንስ ከ10 ደቂቃዎች በፊት ወደ ችሎቱ ቦታ ይሂዱ። ማስታወቂያዎን ለተቀባዩ ያሳዩ። ካልተገኙ ወይም ካልተሳተፉ የችሎት መብትዎን ሊያጡ ይችላሉ።

- ሰነድዎን ወደ ችሎቱ ይዘው ይምጡ።

ምስክር ለመጠቀም ካቀዱ፣ መርሐግብር በተያዘለት የችሎት ጊዜ ይመሰክራሉ። ችሎቱ የሚካሄድበትን ሰዓት እና ቀን እና እንዴት መሳተፍ እንደሚችሉ ለምስክርዎ ይንገሩ።

- ምስክሩ በማስታወቂያው ውስጥ ያለውን ተመሳሳይ መመሪያ ይከተላሉ (ሊገኙ የሚችሉበትን ስልክ ቁጥር ማቅረብ፣ የጥሪ ኮድ መጠቀም ወይም ወደ የችሎት ቦታ መሄድ)።
- በስልክ የሚሳተፉ ከሆነ፣ ስልካቸው ጥሩ ተቀባይ እንዲኖረው እና ስልካቸው ከታገደ የደዋይ መታወቂያ ጥሪ መቀበል መቻል እንዳለበት ለምስክርዎ ይንገሯቸው። ምሥክርዎ ሊገኙ የሚችሉበት ቁጥር ይኑርዎት።

ዳኛው ችሎቱን ይቀዳል። ዳኛው የሚጀምሩት በወገኖቹ መካከል ያሉትን ችግሮች በመለየት እና በችሎቱ ወቅት ምን እንደሚከሰት በመግለጽ ነው። ዳኛው የችሎት ጥቅሉን (እና ሌሎች የደረሱ ሰነዶችን) ይመረምራሉ እና ምን እንደ ማስረጃው እንደሚቀበሉ ይወስናሉ።

አስተዳደራዊ ችሎት አስተባባሪው ብዙዉን ጊዜ የDSHS ጉዳይ መጀመሪያ ይወክላል። እያንዳንዱ አካል የራሱን ምስክሮች በመጥራት በሌሎች ወገኖች የተጠሩትን ምስክሮች መጠየቅ ይችላል። ምስክሮች በቃል መሐላ ወይም በማረጋገጫ ይመሰክራሉ። ዳኛውም ጥያቄዎችን ሊጠይቁ ይችላሉ።

ከችሎቱ በኋላ ዳኛው የችሎት መዝገቡ ከተዘጋ 16 ቀናት በኋላ በደብዳቤ የሚላክልዎትን ውሳኔ ይወስናሉ።

በውሳኔው ካልተስማሙ፣ ውሳኔውን ይግባኝ ለማለት የተቀመጡ መመሪያዎች በዳኛው ትዕዛዝ መጨረሻ ላይ ይሆናሉ።